

# ሀና

- ሀና  ሕልቃና ከሚባል እስራኤላዊ ካህን (ሌዋዊ) ጋር ተጋብታ ትኖር ነበር።  በዚያን ዘመን እግዚአብሔር አንድ ሰው ከአንድ በላይ ሚስት እንዲኖረው ይፈቅድ ነበር። ታዲያ ብዙ ጊዜ የአንድ ሰው ሚስቶች በሆኑት ሴቶች መካከል ስምምነት አይታይም ነበር። በሕልቃና ቤተሰብም ከዚህ የተለየ ነገር አይታይም ። ፍናና ተብላ የምትጠራው  የሕልቃና ሌላኛዋ ሚስቱ ልጆች ሲኖሯት ሀና ግን ምንም ልጅ አልነበራትም። በዚህ ምክንያት ሀዘኗ ከባድ ነበርና ልጅ መውለድ በጣም ትፈልግ ነበር። ከሀዘኗ የተነሳም ምግብ መመገብ አትችልም ነበር። ፍናናም በሀና መካንነት ታፌዝ ነበር። የሀናንም ሕይወት ይበልጥ በሀዘንና በምሬት የተሞላ እንዲሆን አደረገችው።

- የሕልቃና ቤተሰብ በዓመት አንድ ጊዜ ወደሴሎ እግዚአብሔርን ለማምለክ ይሄድ ነበር። ታዲያ ሀና በዚያ ስፍራ ከመደሰት ይልቅ በታላቅ ሀዘን ሆና ምግብ አትበላም፣ ምንም አይነት መጠጥም አትጠጣም ነበር። ሕልቃናም ሊያፅናናት ሞከረ። ሀናም የእግዚአብሔር ድንኳን ወዳለበት ስፍራ ሄደች። እግዚአብሔርንም ወንድ ልጅ እንዲሰጣት በፀሎት ለመነችው። እግዚአብሔር ልመናዋን ሰምቶ ይህን ልጅ የሚሰጣት ከሆነ ለእግዚአብሔር መልሳ እንደምትሰጠውና በራሱ ፀጉርም ላይ ምላጭ እንደማይደርስበት በእግዚአብሔር ፊት ተሳለች። ይህ አይነቱ ውሳኔ የናዝራዊነት መሀላ ይባላል። ሀና ስትፀልይ የምታሰማው ድምፅ አልነበረም። ከንፈሮቿ ግን ይንቀሳቀሱ ነበር። በዚያን ጊዜ የነበረው ሊቀ ካህንና ፈራጅ ኤሊም የሀናን ሁኔታ ሲመለከት የሰከረች መሰለው። ስለዚህም ጠራትና የምትጠጣውን መጠጥ መጠን እንድትቀንስ ነገራት። እርሷም ምንም ስካር እንደሌለባትና ከሀዘኗ የተነሳ ልቧን በእግዚአብሔር ፊት እያፈሰሰች እንዳለች ነገረችው። ይህን ስትነግረውም ችግሯ ምን እንደሆነ ገባው። ስለዚህም እግዚአብሔር እንደፀለየሽው ወንድ ልጅ ይሰጣሻልና በሰላም ሂጂ አላት።

- ሐና የካህኑን የኤሊን ቃል አመነች። ከዚያን ሰዓት ጀምሮም የተለወጠች ሴት ሆነች። ያ ሀዘኗ ጠፋ። ካህኑ እንዳላት ልጅ እንደምትወልድ በልቧ ስላመነች በጣም ደስተኛ ሴት ሆነች። ፍናና ብታላግጥባትና ብትስቅባትም እንደገና ሐዘንተኛ የመሆን ነገሯ አበቃ። ልጅ እንደምትወልድ ታውቅ ነበርና።

- በሴሎ እግዚአብሔርን አምልከው ካበቁ በኋላ ራማ ወደሚገኘው ቤታቸው ተመለሱ። በዚያም ወንድ ልጅን ወለደች። ስሙንም ሳሙኤል ብላ ጠራችው። የስሙ ትርጉምም፣ “እግዚአብሔር ይሰማል፣” ማለት ነው።

- በተከታዩ አመት ወደሴሎ እግዚአብሔርን ለማምለክ ሲጓዙ ሀና ግን ከሕፃኑ ጋር በቤቷ ቀረች። እንዲህም አለች፣ “ጡት አስከሚጥል ድረስ ከእኔ ጋር አቆየዋለሁ። ከዚያም በእግዚአብሔር ቤት ለሁልጊዜ ይሆን ዘንድ ለእግዚአብሔር እሰጠዋለሁ።” ሳሙኤልም አድጎ ጡት ከጣለ በኋላ ሀና ከእርሷ ጋር እግዚአብሔርን ወደምታመልከበት ወደሴሎ ይዛው ሄደች። ለእግዚአብሔር የምታቀርበውን መስዋዕትም ይዛ ነበር። ኤሊንም ስታየው ከዚህ በፊት ስለልጅ ስትፀልይ የነበረችው እሷ እንደነበረች አስታወሰችው። ሳሙኤልንም በኤሊ እግር ስር እንዲያድግ በእግዚአብሔር ቤት ትታው ተመለሰች። ሳሙኤል መላ ሕይወቱ ለእግዚአብሔር የተለየ ሆነ። ስለዚህም በሴሎ ሳሙኤልን ለእግዚአብሔር ለመስጠት የገባችውን ቃሏን ጠበቀች።

- ሳሙኤል በሴሎ እግዚአብሔርን በሚያገለግልበት ጊዜ ሀና አልረሳቸውም። ሁልጊዜም ታስበው ነበር። እድገቱ በጨመረ ቁጥርም ከእርሱ ሰውነት ጋር የሚመጣጠን ልብስ በየዓመቱ ይዛለት ትመጣ ነበር። እግዚአብሔርም በተጨማሪ ልጆች ባረካት። እርሷና ሕልቃና ሶስት ተጨማሪ ወንዶች ልጆችና ሁለት ሴቶች ልጆችን ወለዱ።

*የሀናን ታሪክ በ1ኛ ሳሙኤል ምዕራፍ 1 እና 2 ውስጥ ማንበብ ትችላላችሁ።*